ሳስመግባት መግባት

(አብርሃም ሺበሺ)

ብዙ ሠዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ለመምከርና የሆነ አንድ ውሳኔ ላይ ለመድረስ በአንድነት ይሠባሰባሉ፡፡ አንዳንዶች ለመልካም ነገር ይሠባሰባሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ለክፉ ነገር፡፡ ያም ሆነ ይህ በአንድነት መሠባሰቡ ጥሩ ነገር ነው፡፡ ታላቁ መጽሐፍስ "ውንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ እንሆ መልካም ነው እንሆም ያማረ ነው" አይደል የሚለው? ዋናው ጉዳይ ግን መሠባሰባቸው ሳይሆን የሚሠባሰቡበት ጉዳይ ነው፡፡ የሠው ትዳር ለማፍረስ ተሠብስበው የሚመክሩ እንዳሉ ሁሉ የፈረሱ ትዳሮችን ለማቅናት ተሠብስበው የሚመከሩም አሉ፡፡ ጻድቁን ክርስቶስን ሠቅለው ወንጀለኛውን በርባንን ለማስፈታትም ቢሆን የመከሩ ነበሩ፡፡ ለማንኛውም ይህን እዚህ ጋር ልቋጨውና ወደተነሳሁበት ርዕስ ልመለስ፡፡

አንዳንድ ጊዜ ከሌሎች ሠዎች ጋር ሳስመግባት አስቀድመው ከራሳቸው ጋር የሚግባቡ ሠዎች ያጋጥሙኛል፡፡ ከነዚህ ሠዎች ጋር በጭራሽ መግባባት አይቻልም፡፡ በጭራሽ!! ምክንያቱም ሳስመግባት አስቀድመው ከራሳቸው ጋር ተግባብተዋል፡፡ እናንተ ቀኝ ስትሉ እነሱ ግራ ይላሉ፡፡ እናንተ ዛሬ ይሁን ስትሉ እነሱ ደግሞ አይ! ነገ መሆን አለበት ይላሉ፡፡ ምናልባት እናንተ ለመሸነፍ ብላችሁ ሃሳባችሁን ወደነሱ ሃሳብ ለማስጠጋት ከሞከራችሁ እንኳ ተመልሰው የናንተን ሃሳብ ደጋፊ ሆነው ታገኟቸዋላችሁ፡፡ የነዚህ ሠዎች ዋነኛ ዓላማቸው አለመግባባት ብቻ ነው፡፡ ወይም ደግሞ አለመግባባትን በመፍጠር አሸናፊ መሆን ነው፡፡ እንዲህ ቢሉኝ እንዲህ እላቸዋለሁ በሚል ፎርሙላ ተዘጋጅተው ነው የሚመጡት፡፡ በናንተ ሃሳብ ላይ ምንም አይነት ነቀፊታ እንደሌለባቸው ለማሳየት ሲፈልጉ ደግሞ "እሱ ….. ግን" እያሉ ያወሯችኋል፡፡ ሳስመግባት መግባት ይሏችኋል እንዲህ ነው!!

**ሁሉ አዋቂ**

የራሴ የሚለው ከሌላው በልጦበት

ሁሉ ፈቃድ አለው የሚሟገትለት፡፡

ምክርና ተግሳጽ ቀሎበት በአይኑ

ሁሉ አዋቂ ነው "አይ ኖ" የዘመኑ፡፡

የግጥም ምንጭ፡ የሞት ሽለቆ /የግጥም መድብል/ ከወርቁ ለገሰ ጌታሁን